| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ዐምድ ። " |
| ርእስ ፤ | "ሐፄጌ" |
| ደራሲ ፤ | ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ (አለቃ) ። |
| ዕለት ፤ | ግንቦት ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-002 ። |
| ማስታወሻ ፤ | ከ"መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ። " ፡ 1948 ፡ ዓ.ም. ፥ ከገጽ ፡ 457 ፡ የተቀዳ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ዐምድ ።

## History Column | colonne d'histoire

# "ሐፄጌ ። "

ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ (1862-1936 ፡ ዓ.ም.) ።

(ከ"መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ። " ፡ ገጽ ፡ 457 ፡ የተቀዳ ። )

http://www.gzamargna.net/html/gzMezgebeQalat457.html

---

**ሐፄጌ ፤ (ማእከላይ ፡ ስም)** ፤ ዘይቤው ፡ ዕጨ ፣ ዕጨጌ ፤ ሱታፌ ፡ ንጉሥ ፤ ባለሚሶ ፡ መንግሥት ። ምስጢሩ ፥ ሊቀ ፡ ሀገር ፣ ሊቀ ፡ ካህናት ፣ ርእሰ ፡ አድባራት ፡ ወገዳማት ። ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ኒቅያ ፡ ሕግ ፡ ትምርቱንና ፡ ንጽሕናውን ፣ ጠባዩንና ፡ አናዎሩን ፣ አስተዳደጉን ፡ አይታ ፣ መርምራ ፥ ይደልዎ ፡ ብላ ፡ መርጣ ፣ መስክራ ፡ ባልሾመችው ፥ ሌሎች ፡ ከወገናቸው ፡ መርጠው ፡ በሚሾሙት ፥ ቋንቋውን ፡ በማታውቀውና ፡ ቋንቋዋን ፡ በማያውቅላት ፡ በባዕድ ፡ በንግዳ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጳጳስ ፡ ታዞ ፡ ተናዞ ፡ መኖርን ፡ ሰለ ፡ ወደደች ፤ ፪ኛም ፡ ክብሯንና ፡ መንበረ ፡ ክብሯን ፡ አካታ ፡ ፈጽማ ፥ ይቅርብኝ ፡ ብላ ፡ ለባዕድ ፡ መስጠትን ፡ ስለ ፡ ጠላች ፥ አፍኣዊ ፡ ስሙን ፡ መለካዊ ፡ ወይም ፡ ባስልዮስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ሐፄጌ ፡ ብላዋለች ፡ እንጂ ፥ ውስጣዊ ፡ ስሙ ፡ ጳጳስ ፣ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ነው ። ጳጳስ ፡ ሲታጣም ፥ በግልጥ ፡ የጳጳስ ፡ ሥራን ፡ እየሠራ ፡ አቡንና ፡ ዕጨጌ ፡ ይባላል ፤ ጳጳስም ፡ ቢኖር ፥ ላገሩ ፡ እንግዳ ፥ ለሕዝቡ ፡ ባዳ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አፈ ፡ ድዳ ፣ ቀንደ ፡ ጐዳ ፡ መስሎ ፥ ያቀረቡለትን ፡ ቅስና ፣ ዲቁና ፡ ከመሾም ፡ በቀር ፡ ሊፈርድና ፡ ሊተች ፥ ሊሰብክ ፡ ሊያስተምር ፡ አይችልምና ፥ በሕዝብና ፡ በካህናት ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑ ፣ መብቱ ፣ ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ወትሮ ፡ የዕጨጌው ፡ ነው ። **«ወፈታሒሰ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፤ አው ፡ ኤጲስቆጶስ ፤ አው ፡ ዘአትለውዎ ፡ እሙንቱ ፡ ወረሰይዎ ፡ ህየንቴሆሙ ፡ በእንተ ፡ ፍትሕ ። ይኩን ፡ ድጉኑ ፡ ልሳን ፡ ወዘየአምር ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ እንተ ፡ ኢትትከሀል ፡ ልሳነ ፡ ሰብእ ፡ ሢመቱ ፡ በዘይትናገሩ ፡ በበይናቲሆሙ»** ፡ (ፍ.ነ. ፥ ፵፫) ። በ"ፅግዕ" ፡ እና ፡ በ"ፅጋዕ" ፡ ዘይቤም ፡ ሲፈቱት ፥ **«ወምስማካሰ ፡ ለመንግሥትክሙ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ»** ፡ እንዳለው ፡ ሹሉ ፡ (ቄር.) ፥ መጨጊያ ፣ መከዳ ፡ ያሰኛል ። ዕጨግናን ፡ ከጽጽስና ፡ አዛምዶ ፣ አዋሕዶ ፣ አጣምሮ ፣ አስተባብሮ ፡ ያሳያል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መከዳ ፥ ንጉሡን ፡ አማኽለው ፥ አቡኑ ፡ በቀኝ ፥ ዕጨጌው ፡ በግራ ፡ በመቀመጣቸው ፡ ይታወቃል ። አቡን ፡ ሲታጣ ፡ ግን ፥ ቀኙ ፡ የዕጨጌ ፡ ነው ። ዕጨጌነትም ፡ የተዠመረ ፡ ባ፲፪፻፷፫ ፡ (፶፫) ፡ ዓመት ፥ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ ቀብተው ፡ ባነገሡ ፡ በዳግማይ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ርሳቸውም ፥ በናታቸው ፡ የነገሥታት ፡ ወገን ፥ የይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ያክሥት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የናት ፡ ወንድም ፥ አጎት ፤ ወዲህም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ፊት ፡ በሕግ ፡ ቀሰው ፥ በኋላ ፡ መንኵሰው ፡ አቡን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ የማይገባ ፡ መስሏቸው ፡ «አቦ ፡ ብልጎት ፥ ዕጨግነት ፡ ከሚስት» ፡ ብለዋቸዋል ። ዳግማይ ፡ ማለትም ፥ በ፳ኛው ፡ መቶ ፥ ይህን ፡ ሐዲስ ፡ ስም ፥ «ተክለ ፡ ሃይማኖት» ፡ መባልን ፥ እንደ ፡ ያዕቆብ ፥ በጌታ ፡ ቃል ፡ ለተሰየሙት ፡ ለጻድቁና ፡ ለቅዱሱ ፥ ለታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ እንጂ ፥ ባ፲ኛው ፡ መቶ ፡ መንግሥትን ፡ ከድልነዓድ ፡ ወስዶ ፡ መዠመሪያ ፡ ከዛጔ ፡ ወገን ፡ ለነገሠው ፡ መራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለተባለው ፡ ለላስታው ፡ ንጉሥ ፡ አይደለም ። በጻድቁና ፡ በዕጨጌው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ካ፳፻፶ ፡ ቢበልጥ ፡ እንጂ ፡ አያንስም ፡ (ታሪክና ፡ ገድል) ። ጳጳስን ፡ እይ ፨

---


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።